# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

## ሁለተኛው ትውልድ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም
### የተቋማት ጤና አጠባበቅ ፓኬጅ

ሐምሌ 2007 ዓ.ም
አዲስ አበባ

**ማውጫ**

1. መግቢያ ........ 3

2. ዓላማ ........ 3

2.1. አጠቃላይ ዓላማ ........ 3

2.2. ዝርዝር አላማዎች ........ 3

3. ቁልፍ መረጃዎች ........ 4

3.1. በትምህርት ቤት የንፅህና አጠባበቅ ........ 4

3.2. የወፍጮ ቤት ንፅህና አጠባበቅ ........ 6

3.3. የጤና ኬላ ንፅህና አጠባበቅ ........ 7

3.4. የኃይማኖት ተቋማት የቆሻሻ አወጋገድ ........ 12

4. የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራትና አተገባበር ........ 12

4.1. ህብረተሰቡንና የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በመለየት ስለ ፓኬጁ ምንነትና አተገባበር ማስተዋወቅ እና ማነቃቃት ........ 12

4.2. ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር (ደረጃ ሶስት የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች፣ የልማት ቡድን መሪዎች ወዘተ) አስፈላጊ መረጃዎችን ማሰባሰብ ........ 13

4.3. ውጤቱን ለሁሉም ተቋማት መግለጥና በጋራ የሥራ ዕቅድ ማውጣት ........ 13

4.4. ትምህርት ቤት ክበባት ማጠናከርና ከየተቋማቱ ለተውጣጡ ባለድርሻ አካላት ስልጠና መስጠት ........ 13

4.5. ለፓኬጁ ሥራ ደጋፊ ሊሆኑ ከሚችሉ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ የጤና ልማት ሰራዊት፣ ተቋማት፣ ማህበራዊ ተቋማት፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በቅንጅት መሥራት ........ 14

4.6. ዕቅድ ማዘጋጀትና በትብብር መሥራት ........ 14

4.7. የተቋማቱን ማህበረሰብ በመቀስቀስ፣በማስተማር፣ተሳትፎውን በማሳደግ ቀጣይ የጸባይ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ትምህርት ተግባራት በመለየት ማከናወንና ተከታታይነት ያለው ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ........ 15

4.8. ሠርቶ ማሳያ ዘዴ በመጠቀም ማህበረሰቡ በራሳቸው እንዲሠሩ ማስቻል ........ 15

4.9. ምርጥ ተሞክሮ መለየት፣ መቀመርና ማስፋት ........ 15

4.10. የማነቃቂያ ዘዴዎች በመጠቀም የማህበረሰቡን ባለቤትነት ማጠናከር ........ 15

4.11. አካባቢያዊና ሕጋዊ ደንቦችን መጠቀም ........ 15

4.12. የክትትልና የጉብኝት ሥራዎች ማካሄድ፣ ........ 16

5. ከጤና ጣቢያ ጋር አብሮ መስራት ........ 16

6. የሚጠበቁ ውጤቶች ........................................ 16
7. ክትትልና ግምገማ ........................................ 17
7.1. ክትትል ........................................ 17
7.2. ግምገማ ........................................ 17
7.3. የፓኬጅ ጠቋሚዎች /indicators/ ........................................ 18

# 1. መግቢያ

በሀገራችን አብዛኛው ሐብረተሰብ የሚኖረው በገጠር ቀበሌዎች እንደሆነ ይታወቃል፡፡ የገጠሩ ነዋሪ ለበርካታ ዘመናት ከመሰረታዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ርቆ ይኖር እንደነበረ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡ የገጠሩ ህብረተሰብ ገቢ እየጨመረ መምጣትና የመሰረተ ልማቶች በሁሉም የገጠር ቀበሌዎች ለማዳረስ የተደረገው ጥረት ተደማምሮ በገጠሩ ቀበሌዎች የአገልግሎት መስጫ  አነስተኛና መካከለኛ ተቋማት እየተስፋፉ መጥተዋል፡፡ ከነዚህም ተቋማት መካከል ትምህርት ቤት፣ጤና ኬላ፣ወፍጮ ቤት፣እንዲሁም የሐይማኖት ተቋማት ወዘተ…ይገኙበታል፡፡

ትምህርት ቤቶች ብዙ ልጆችና ወጣቶች የሚሰበሰቡባቸውና የሚውሉባቸው እንዲሁም ብዙ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉበት ተቋም በመሆኑ ጤናው የተጠበቀና አርዓያ ሊሆን ይገባዋል፡፡ በትምህርት ቤት የሚሰሩ የጤና ፕሮግራሞች በተማሪዎችና መምህራን አማካኝነት ወላጆችና ህብረተሰቡን ለመለወጥ አይነተኛ መሳሪያ በመሆን ያገለላሉ፡፡ አንድን ትምህርት ቤት የተሟላ ከሚያደርጉተ አገልግሎቶች ውስጥ የንፁህ ውሃ አቅርቦትና አያያዝ፣ መፀዳጃ ቤት መኖርና መጠቀም እንዲሁም ተማሪዎች መሰረታዊ የንጽህና አጠባበቅን በትምህርት ቤት መተግበር ሲቻል ነው፡፡ የእነዚህ አገልግሎቶች በትምህርት ቤቶች አለመሟላት የተማሪዎችን ውጤት መቀነስ እና ከትምህርት ቤት መቅረትን ያስከትላል፡፡ በተለይም ሴት ተማሪዎች የተለየ መፀዳጃ ቤት ከሌላቸው በወር አበባ ጊዜ ከትምህርት ቤት እንዲቀሩ ስለሚገደዱ የሴት ተማሪዎች ቁጥር ይቀንሳል፡፡

በገጠር ቀበሌዎች በአሁኑ ወቅት በመስፋፋት ከሚገኙት ተቋማት አንዱ ወፍጮ ቤት ነው፡፡ በመሆኑም ወፍጮ ቤቶች ባግባቡ ካልተሰሩ፣ንፅህናቸው ካልተጠበቀና የአደጋ መከላከያ ከሌላቸው ለጤና ጠንቅ ሊሆኑ ስለሚችል ሌላው የትኩረት መስክ ነው፡፡ በተጨማሪም የጤና ኬላው ንፅህና አጠባበቅና የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ዘዴው ለሌሎች አርአያ ሊሆን በሚችል መልኩ የተደራጀ መሆን ይኖርበታል፡፡

በገጠር በቀበሌ ደረጃ የሚገኙ የሐይማኖት ተቋማት ንጽህና በተመለከተ እስካሁን ድረስ በቤተሰብ ደረጃ ታሳቢ ባደረገ መልኩ ድጋፍ እተደረገላቸው መቆየቱ ይታወቃል፡፡ሆኖም ግን ከሚሰጡት አገልግሎትና የአማኞች ብዛት አንጻር ሲታይ ሌሎችን በሚያስተምር መልኩ ትኩረት ተሰጥቶት መሰራት አለበት፡፡

ስለዚህ በገጠር ቀበሌዎች የእነዚህን ተቋማት ጤና ለመጠበቅ ይረዳ ዘንድ ይህን ፓኬጅ በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ውስጥ ማካተት አስፈልጓል፡፡

# 2. ዓላማ

## 2.1. አጠቃላይ ዓላማ

በገጠር ቀበሌ ደረጃ የሚገኙ ተቋማትና ድርጅቶች ጤናማ የሥራ ቦታ እንዲሆኑ በማድርግ ተገልጋይ ህብረተሰብ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ የጤና ችግሮችን መከላከልና መቆጣጠር፡፡

## 2.2. ዝርዝር አላማዎች

- በትምህርት ቤት የሚገኘው ማህበረሰብ ስለ አካባቢ ጤና፣ በሽታዎችና አደጋዎች ያለውን ግንዛቤ፣ እውቀትና ክህሎት እንዲያዳብር መደገፍ

- ❖ ትምህርት ቤቶች ንፅህናው የተጠበቀ የውኃ አገልግሎት እንዲኖራቸው ለማገዝ
- ❖ ትምህርት ቤቶች ንፅህናው የተጠበቀ እና በፆታ የተለየ መፀዳጃ ቤት እንዲኖራቸው ለማገዝ
- ❖ ተማሪዎች ከመፀዳጃ ቤት መልስ እጃቸውን በአግባቡ እንዲታጠቡ ለማድረግ
- ❖ በወፍጮ ቤት ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎችንና የጤና ጠንቆችን ለመቀነስ
- ❖ ከጤና ኬላ/ጤና ጣቢያ የሚወጡ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻዎች በአግባቡ እንዲያዙና እንዲወገዱ ለማድረግ እንዲሁም አማራጭ ቴክኖሎጂ እንዲኖር ድጋፍ ማድረግ
- ❖ የሐይማኖት ተቋማት ንፅህናው የተጠበቀ የውኃ አገልግሎት እንዲኖራቸው ለማገዝ
- ❖ የሐይማኖት ተቋማት ንፅህናው የተጠበቀ እና በፆታ የተለየ መፀዳጃ ቤት እንዲኖራቸው ለማገዝ

# 3. ቁልፍ መረጃዎች

## 3.1. በትምህርት ቤት የንፅህና አጠባበቅ

አንድ ት/ቤት ተማሪዎች በትምህርታቸው የተሻሉና ብቁ ዜጋ እንዲሆኑ ለማስቻል አቅም በፈቀደ መጠን የሚከተሉትን አገልግሎቶች እንዲያሟላ ለት/ቤቱ ማህበረሰብ ትምህርት መስጠትና ማንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡ መሰረታዊ አገልግሎቶችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

**የመማሪያ ክፍሎች ሁኔታ**

- ❖ ህንፃው አደጋ የማያደርስ መሆን አለበት (ያልተሰነጣጠቀ)
- ❖ ክፍሎች በቂ እና ንፁህ አየር የተፈጥሮ ብርሀን የሚያስገቡ  መስኮቶች ሊኖሩት ይገባል
- ❖ መስኮቶች ሁልጊዜ መከፈት ይኖርባቸዋል
- ❖ ወለሉም ሆነ ግድግዳው በቀላሉ ሊፀዳ የሚችልና ንፅህናው የተጠበቀ መሆን አለበት

**የንፁህ ውኃ አቅርቦት**

ት/ቤቱ በቂና ንፅህናው የተጠበቀ ውሃ ሊኖረው ይገባል፡፡ ትምህርት ቤቱ ውሃ ከሌለው ከት/ቤቱ አስተዳደር፣ወመህ እና ድጋፍ ከሚሰጡ አካላት ጋር በመቀናጀት ችግሩ የሚቃለልበትን  መንገድ መፈለግ፡፡  የንጹህ ውኃ አቅርቦት ያለው ከሆን የሚከተሉትን መሰረት በማድረግ ማስተማር ይገባል፡፡

- ❖ ውሃው የታከመ፣ ከጎጅ ንጥረ ነገሮች እና በሽታ ከሚያመጡ ጀርሞች ነጻ መሆኑ በላብራቶሪ እንዲመረመር፣
- ❖ የውሃ ማጠራቀሚያ ያለው ከሆነ ቢያንስ በሴሚስተር አንድ ጊዜ መታጠብና መታከም እንዳለበት፡፡
- ❖ በተማሪዎች ቁጥር በቂ መጠን ያለው ውሃ እና አመች ቦታ ላይ የመቅጃ ቦታ እንዲዘጋጅ
- ❖ ተማሪዎችና መምህራን በራሳቸው ንፅህናው የተጠበቀ ውሃ መጠጫ እንዲጠቀሙ

❖ ውሃው የሚሰራና ሁል ጊዜ ክፍት መሆን እንዳለበት

❖ በተማሪዎች ቁጥር በቂ መጠን ያለው ውሃ እና አመች ቦታ ላይ የመቅጃ ቦታ ሊዘጋጅ ይገባል

❖ አንድ የውሃ ቧምቧ/ፎሴት ለ100 ተማሪዎች ያገለግላል በሚል ስሌት መዘጋጀቱን

**መፀዳጃ ቤት**

ት/ቤቱ በቂና ንፅህናው የተጠበቀ መፀዳጃ ቤት ሊኖረው ይገባል፡፡ትምህርት ቤቱ መፀዳጃ ቤት ከሌለው ከት/ቤቱ አስተዳደር፣ወመህ እና ድጋፍ ከሚሰጡ አካላት ጋር በመቀናጀት ችግሩ የሚቃለልበትን መንገድ መፈለግ፡፡ መፀዳጃ ቤት ያለው ከሆን የሚከተሉትን መሰረት በማድረግ ማስተማር ይገባል፡፡

❖ የመፀዳጃ ቤቱ ከመማሪያ ክፍሎች 30 ሜትር ርቀት ላይ መሠራቱንና የነፋስ አቅጣጫ የተከተለ መሆኑን

❖ ለሴቶች የተለየ ንፅህናው የተጠበቀ መጸዳጃ ቤት መኖር እንዳለበት

❖ የመፀዳጃ ወረቀት ማጠራቀሚያ ቅርጫት መዘጋጀትና ሲሞላ ወዲያው መወገድ እንዳለበት

❖ ስለ መፀዳጃ ቤቱ ንፅህና አጠባበቅ (ወለሉና ግድግዳው በወቅት ተከታትለው ማፅዳታቸውን)

❖ መፀዳጃ ቤቱ በማንኛውም ወቅት ለተጠቃሚዎች ክፍት መሆን እንደሚገባው

❖ አንድ መቀመጫ ለሴት ተማሪዎች አንድ ለ35 እና ለወንድ ተማሪዎች አንድ ለ100 አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል በሚል ታስቦ እንዲዘጋጅ

❖ ንፅህናው የተጠበቀ የእጅ መታጠቢያ (ሳሙና፣ኦሞ ወይም አመድ) ከመፀዳጃ ቤቱ አጠገብ መኖር እንዳለበት

❖ በእጅ መታጠቢያው ውስጥ ውኃ በየጊዜው እንዲሞላ

**መሠረታዊ የግል ንጽህና (ሀይጅን)**

ተማሪዎችም ሆነ መምህራን ስለ መሰረታዊ የግል ንፅህና (ፊት፣ ፀጉር፣ ልብስ፣ በወር አበባ ጊዜ ስለሚደረግ ንፅህና ወዘተ) አጠባበቅ በተለይም ስለ እጅን በወሳኝ ሠዓታት ትኩረት በማድረግ በግልና መኖሪያ ቤት ንፅህና አጠባባቅ ፓኬጅ የተቀመጠውን መሰረት አድርጎ ማስተማር ይገባል፡፡ በተለይም ተማሪዎች ላይ በሳምነት አንዴ የግል ንፅህና ቁጥጥር እንዲኖር ማስተማር፡፡

**የፈሳሽና ደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ**

❖ ከእጅ መታጠቢያ እና ውሃ መጠጫ አካባቢዎች የሚፈሰውን ውሃ በአግባቡ ለማስረግ የተዘጋጀ ጉድጓድ እንዲኖር

❖ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃው በአግባቡ የሚሰራና ንፅህናው የተጠበቀ እንዲሆን

❖ ለደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ የሚውል ጉድጓድ/የደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ/ እንዲኖር

❖ በየክፍሉ የወረቀትና ሌላ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ እንዲዘጋጅ

- የተሰበሰበውን ቆሻሻው በሳምንት አንድ ጊዜ በተገቢው ጥንቃቄ መቃጠል/መወገድ እንዳለበት

- በየሳምንቱ በፕሮግራም የተያዘ የግቢ ፅዳት እንዲኖር

**በሽታዎችን መከላከልና መቆጣጠር**

በበሽታዎች መከ/መቆ/ፓኬጅ በተቀመጠው መሰረት ለመምህራንና ተማሪዎች ስለ ዋና ዋና ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ማስተማር

- በትምህርት ቤት ውስጥ ተላላፊ በሽታና ሌሎች የጤና ችግሮች ያለባቸውን ተማሪዎች መለየትና ማከም

- በትምህርት ቤት ውስጥ የትራኮማ መከላከልና መቆጣጠር ሥራዎችን ማከናወን

## 3.2. የወፍጮ ቤት ንፅህና አጠባበቅ

በአሁኑ ወቅት በገጠር ቀበሌዎች እየተስፋፋ የሚገኝ በመሆኑ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ ለባለቤቶችና ተቀጥረው ለሚሰሩ ሠራተኞች ስለ ንፅህና አጠባበቅና አደጋ መከላከል ላይ ትምህርት መስጠት ይገባል፡፡ የሚጠበቀውን መመዘኛ ሳይሟላ ከተገኘ ለማሻሻል በጋራ ሙከራ ከተደረገ በኂላ የክልሉን የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ህግ ተጠቅሞ የማስተካከያ ርምጃ መውሰድ ይገባል፡፡ ትምህርቱና ቁጥጥሩ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ያተኩራል፡፡

- ወፍጮ ቤቱ ሲተከል መኖሪያ ቤቶችን በድምፅ የማይረብሽ ስለመሆኑ፣

- ወፍጮ ቤቱ በቂ የተፈጥሮ ብርሀንና የአየር ዝውውር እንዲኖረው (በቂ መስኮቶች እና በሽቦ ወንፊት የተሸፈኑ ግድግዳዎች ዙሪያውን መዘጋጀቱን)

- የብናኝ ማስወጫ ቱቦ ስለመኖሩ፣

- ንፅህናው የተጠበቀ የስራ ልብስ (ቱታ)፣ኮፍያ(ቆብ)፣ ጫማ፣ከተቻለ የድምፅ መከላከያና መነፀር ስለመኖሩ፣

- ወለሉ በቀላሉ ሊፀዳ የሚችል (ስሚንቶ የሆነ) ፣ንፅህናው የተጠበቀ፣ ዘይትና ቅባት ያልፈሰሰበት ስለመሆኑ፣

- ለፈጭዎችና አስፈጭዎች ላይ አደጋ እንዳያደርስ ሆኖ ችንጋው የተከለለ (የታጠረ) ሰለመሆኑ፣

- የጭነት አህያ፣በቅሎ ወይም የፈረስ ማሰሪያ ከሚዛን አካባቢ ራቅ ብሎ ማሰሪያና መቆያ አጥር እንዲኖረው ማድረግ፣

- የፍሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ በአግባቡ መዘጋጀቱን

- በወፍጮ ቤቱ የእህል አቅርቦትና ማስቀመጫ ክፍል ካለው ከቆርጣሚ እንስሳት ነፃ ስለመሆኑ

- በወፍጮ ቤቱ ውስጥ እንስሳት እንዳይገቡ መደረጉን

- ንፅህናው የተጠበቀ እና ለተጠቃሚዎች በማንኛውም ሠዓት ክፍት ሆኖ አገልግሎት የሚሰጥ መፀዳጃ ቤት መኖሩን፣

- ዝናብና ሌላ ፍሳሽ ቆሻሻ ወደ ውስጥ የማያስገባ
- ወፍጮ ቤቱ ውስጥ ሲገቡ የማያፍንና የማይሸት መሆኑን

## 3.3. የጤና ኬላ ንፅህና አጠባበቅ

### የጤና የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ

ጤና ኬላ ህብረተሰቡ የሚጠቀምበትና እንደ ሞዴል የሚታይ በመሆኑ መሰረታዊ የሆኑ ለንፅህና አጠባበቅ የሚያስፈልጉ እንደ ንፁህ ውሃ፣መፀዳጃ ቤት፣የእጅ መታጠቢያ፣የፈሳሽና ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ሊኖረው ይገባል፡፡

በመሆኑም የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ በራሷ የሚሟሉትን ማሟላት እና ከአቅሟ በላይ የሆኑትን ከቀበሌው አስተዳደር፣ከህብረተሰቡ፣ከጤና ጣቢያውና ከሌሎች ድጋፍ ሊያደርጉ ከሚችሉ አካላት ጋር በመተባበር መሥራት ይጠበቅባታል፡፡

- ጤና ኬላው ንፅህናው የተጠበቀ፣ሽታ የሌለው፣ እቃዎቹ በአግባቡ የተደረደሩ ንፅናቸው የተጠበቀ፣ማድረግ
- የሚሰራ፣ንፅህናው የተጠበቀና ሁል ጊዜ ክፍት የሆነ መፀዳጃ ቤት መኖር አለበት
- ጤና ኬላው የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ የሚሠራ የደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ (Incinerator) ሊኖረው ይገባል፡፡ ከሌለው ግን ርቀቱን የጠበቀና የንፋስ አቅጣጫን ግምት ውስጥ ያስገባ የቆሻሻ ጉድጓድ ማሰራት የግድ ነው፡፡
- የቧንቧ ውኃ ከሌለ ከንፁህ ቦታ የተቀዳ እና በንፁህ እቃ የተቀመጠ ውኃ ሊኖር ይገባል፡፡ የተጠበቀ የውሃ መገኛ ከሌለ የዝናብ ውሃን በንፁህ እቃ በማጠራቀም አክሞ መጠቀም ይገባል፡፡

### ከህክምና የሚወጡ ቆሻሻዎች በጥንቃቄ ካልተወገዱ የሚያስከትሉት የጤና ችግር

በጤና ኬላ የሚሰጡ አገልግሎቶች እየጨመሩ ሲመጡ የሚመረተውም ቆሻሻ አይነትና መጠን አብሮ ይጨምራል፡፡ በመሆኑም እንደማንኛውም ቆሻሻዎች ሁሉ በጥንቃቄ ካልተወገዱ የሚከተሉትን የጤና ችግር ያስከትላሉ፡፡

- በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ ላይ የመቁሰል ወይም ለበሽታ ያጋልጣል (ኤች አይቪ/ኤድስ፣ሄፓታይተስ ወዘተ…)፡፡
- በጤና ኬላው የሚገለገሉ ህሙማን፣ወላዶች፣እና ልዩ ልዩ ተጠቃሚዎችን ለአደጋና ለበሽታ ሊያጋልጥ ይችላል፡፡
- ቆሻሻን በሚያፀዱና በሚያስወግዱ ሠራተኞች ላይ አደጋና የጤና ጠንቅ ይሆናል፡፡
- የአካባቢውን ነዋሪ በተለይ ህፃናትን ለአደጋና ለበሽታ ያጋልጣል፡፡
- የአካባቢ መበከልን ያስከትላል
- ከጤና ኬላ የሚወጡትን ቆሻሻዎች ከሚያስከተሉት ጉዳት አንፃር በሚከተሉት መልክ መክፈል ይቻላል፡፡

**ጉዳት የማያስከትሉ** /Non infectious wastes/፡- ከደምና ሰውነት ፈሳሽ ጋር ንክኪ የሌላቸው እንደ መኖሪያ ቤት አይነት ቆሻሻዎች ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ወረቀት፣ ካርቶን፣ ያልተበከሉ ፕላስቲኮች፣ ብረታብረት፣ ጠርሙስ ወዘተ…

**ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትሉ** /Infectious non- sharp clinical wastes/፡- በምርመራ የምንጠቀምባቸውን፣ በህክምና ወቅትና በመውለድ/ማስወረድ ጊዜ ከሰውነት አካለት የሚወጡ የሰውነት ፈሳሾችን የሚያጠቃልል ሲሆን ከሰው ወደ ሰው/ እንስሳት በሽታን ለማስተላለፍ ከፍተኛ አቅም ያለው ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ደም፣ አክታ፣ መግል፣ ደም የተበከሉ ቁሳቁሶች (ጎዝ፣ ጓንት፣ቁስል ማሸጊያ፣አይቪ) ወዘተ…

**በስለታማ ነገሮች**/Sharp materials/፡- እነዚህ በሰውነት ላይ መቆረጥን ወይም መወጋት የሚያስከቱና በሽታ ከህመምተኛው ወደ ጤነኛ ሰው በቀላሉ ሊያስተላልፉ የሚችሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- መርፌ፣ ምላጭ፣ የጠርሙስ ስባሬ፣ ላንሴት ወዘተ…

**በመውለድና ውርጃ ጊዜ የሚወገዱ የሰውነት አካላት** /Anatomical wastes and Placenta/፡- እነዚህ ቆሻሻዎች የሰው አካል በመሆናቸው ስነምግባር በተሞላበትና የአካባቢውን ወግ በጠበቀ መልኩ መወገድ ያለባቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- የእንግዴ ልጅ፣የወረደ ፅንስ፣ ሞቶ የተወለደ ህፃን

**በመድኃኒቶችና ሪኤጀንቶች**/Pharmaceutical wastes/፡- በዚህ ስር የሚጠቃለሉት አገልግሎት ዘመናቸው ያለፈባቸው መድኃኒቶችና ህክምና መገልገያዎችን ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- መድኃኒት፣ ሪኤጀንቶች

**የቆሻሻ አሰባሰብ፣ አያያዝና አወጋገድ**

የተቀናጀ የቆሻሻ አሰባሰብ፣ አያያዝና አወጋገድ ዋና አላማ በጤና ተቋሙም ሆነ ከተቋሙ ውጭ በዚህ ምክንያት የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ ነው፡፡ በመሆኑም የሌሎች ቆሻሻ አይነቶችን ለማስወገድ የምንጠቀምባቸው ዘዴዎችን መሰረት በማድረግ በሚከተለው መልኩ ሊተገበር ይገባል፡፡

**ሀ. የሚመረተውን የቆሻሻ መጠን መቀነስ** /Waste minimization/፡- ምን ጊዜም በጥቅም ላይ የምናውላቸውን ቁሳቁሶች በአግባቡ በመጠቀመና ያለምክንያት ቆሻሻ ማምረትን በማስወገድ የሚመረተውን ቆሻሻ መቀነስ ያስፈልጋል፡፡

**ለ. ቆሻሻዎችን መለየት**/segrigation/ **እና ማጠራቀም**/Storage/፡- ቆሻሻዎች የሚያደርሱት ጉዳትና የጤና ችግር እንደ ቆሻሻው አይነት የተለያየ ስለሆነ በሚቀመጡበትና በሚያዙበት ወቅት ሊለዩ ይገባል፡፡ ለቆሻሻ ማጠራቀሚያ የምንጠቀምባቸው የተለዩ እቃዎች በምናዘጋጅባቸው ወቅት ከግንዛቤ ሊገቡ የሚገባቸው ነጥቦች

- በየክፍሉ እንደ ቆሻሻው አይነት የተለያዩ ማጠራቀሚያዎች ሊኖሩ ይገባል
- ሌላ ሰው ቀለሙን አይቶ ሊረዳው የሚችል እና ምልክት ሊኖረው ያስፈልጋል
- አደጋ የሚያደርሱትና የማያደርሱት ያልተደበላለቁ
- በሁሉም ጤና ተቋማት ተመሳሳይ የሆኑ

❖ በየጊዜው ክትትል የሚደረግባቸው

❖ ቆሻሻ ከሁለት ቀን በላይ መቆየት የለበትም ነገር ግን የእንግዴ ልጅ፣ሌላ የሰውነት አካላት ወዲያውኑ መወገድ አለባቸው


በጤና ኬላ ውስጥ ለቆሻሻ ማጠራቀሚያነት የምንጠቀምባቸው እቃዎች ቀለም የሚከተሉት ናቸው፡፡

❖ ጥቁር ቀለም ያለው ፦ አደጋ ለማያስከትሉ ቆሻሻዎች

❖ ቀይ ቀለም ያለው፦ አደገኛ ንጥረ ነገሮች (በጤና ኬላ የማይገኙ)

❖ ቢጫ ቀለም ያለው፡ - አደጋ ለሚያስከትሉ ቆሻሻዎች / ስለታማ ነገሮች፣ ከሰውነት የሚወጡ ፈሳሾች፣መድሀኒቶች፣የጨረር ጉዳት የሚያደርሱ ወዘተ…

 ○ ሴፍቲ ቦክስ በዚህ ክፍል የሚመደብ ሲሆን የሚያገለግለው ግን ለስለታማ ነገሮች ማጠራቀሚያ ብቻ ነው፡፡




**የሴፍቲ ቦክስ አያያዝና አጠቃቀም**

ሴፍቲ ቦክስ ማለት በቀላሉ በስለታማ ነገሮች የማይበሳና የማያንጠባጥብ ለስለታማ ነገሮች ማጠራቀሚያ ታስቦ በፋብሪካ የተዘጋጀ ካርቶን ነው፡፡ሴፍቲ ቦክስን በአግባቡ መጠቀም በጤና ባለሙያና በተጠቃሚው ህብረተሰብ ዘንድ ሊደርስ የሚችለውን የጤና ችግር በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሳል፡፡ በመሆኑም ሴፍቲ ቦክስን ስናዘጋጅና ስንጠቀም በሚከተለው መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡

❖ ፋብሪካው ባዘጋጀው ቀላል መመሪያ መሰረት በመከተል ማዘጋጀት

❖ ስለታማ ነገሮችን ከተጠቀምን በኋላ በቀላሉ እጅ ሊደርስበት በሚችል ቦታ ማስቀመጥ

❖ የተጠቀምንባቸውን መርፌ ሳንነቃቅል እና ሳንከድን እንዳለ መክተት

❖ እጅን በሳጥኑ ውስጥ አለማስገባት እና ህፃናትም እጃቸውን እንዳያስገቡ መጠበቅ

❖ ሴፍቲ ቦክሱን እንደገና አለመጠቀም/ቆሻሻውን አራግፎ በድጋሜ ለመጠቀም አለመሞከር


❖ ከመጠን በላይ አለመሙላት/ሲሞላ አንድ አራተኛ ሲቀረው ከድኖ ማስወገድ


❖ ብዙ ለማስያዝ በመፈለግ መነቅነቅ አያስፈልግም

❖ በምናንቀሳቅስበት ወቅት በጓንት መጠቀም/ማጥለቅ

❖ የሞላውን ሴፍቲ ቦክስ በጥንቃቄ ማቃጠል፡፡

❖ ካስወገድን በኋላ እጅን በአግባቡ መታጠብና በአልኮል/ሳቫሎን ማድረቅ





**ሐ. የቆሻሻ ወደ ማስወገጃ ቦታ አወሳሰድ፡-** የተሰበሰበው ቆሻሻ ወደ ማስወገጃ ቦታው በሚጓጓዝበት ጊዜ የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች ማድረግ ያስፈልጋል

❖ ከሰው ንክኪ ተጠብቆ በጥንቃቄ በጋሪ ወይም በሌላ የተሸፈነ ነገር መጓጓዝ ይኖርበታል

❖ ቆሻሻን የሚያጓጉዝ ሰው የጥንቃቄ ልብስ መልበስ ይጠበቅበታል

❖ ቆሻሻን ለማጓጓዝ የምንጠቀምበት እቃ ለሌላ አገልግሎት መዋል የለበትም

❖ ቆሻሻ ማጓጓዣ እቃው ከተጠቀምንበት በኋላ ወዲያውኑ አፅድቶ ለሚቀጥለው አገልግሎት መዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡


**መ. የቆሻሻ ማስወገጃ ዘዴዎች፡-** የማስወገጃ ዘዴዎች እንደየ ቆሻሻ አይነት የሚለያዩ ሲሆን በጤና ኬላ ደረጃ የሚተገበሩት የሚከተሉት ናቸው፡፡

**ስለታም ነገሮች**

ለዚህ አገልግሎት ተብሎ በተዘጋጀ በቆሻሻ ማቃጠያ /Incinerator/ ወይም ጉድጓድ ቆፍሮ በማቃጠል ማስወገድ

**ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ /Infectious/**

በዚህ የሚጠቃለሉ የቆሻሻ አይነቶች በቆሻሻ ማቃጠያ /Incinerator/ ወይም የሰውነት አካል ክፍል የሆኑት (የእንግዴ ልጅ፣የወረደ ፅንስ ያካባቢውን ወግ እና ደንብ ጠብቆ በመቅበር የእንግዴ ልጅና ሌሎች በወሊድና በማስወረድ ጊዜ የሚወጡ ፈሳሾች የሚወገዱበት ሲዘጋጅ በሚቀጥለው ስዕል መሰረት ነው፡፡



**ጉዳት የማያስከትሉ**

እነዚህ አይነት ቆሻሻዎች እንደ ሌሎች የቤትና የቢሮ ቆሻሻዎች በምናስወግድበት መንገዶች ማለትም (በቆሻሻ ጉድጓድ ማቃጠል ወይም በመቅበር፣በኢንሲኔሬተር ማቃጠል) መጠቀም ይቻላል፡፡

**ሠ. የተጠቀምንባቸው እቃዎችን በእንፋሎት ማፅዳት**/Autoclaving/፡- አንዳንድ የአገልግሎት እና የህክምና መስጫ ቁሳቁሶችን ከተጠቀምን በኋላ በሚገባ በማፅዳት ለድጋሚ አገልግሎት ልንጠቀምባቸው እንችላለን፡፡ በድጋሚ ልንጠቀምባቸው የምንችልባቸው እቃዎች እንደ ኪዲኒ ዲሽ፣ ፎርሴፕስ፣ መቀስ፣ኤፕረን፣ሽርጥ፣የማዋለጃ አልጋ ሸፋን ላሲቲክ፣ማስክ፣ወዘተ ናቸው

እነዚህን እቃዎች በእንፋሎት መቀቀያ በ121 ዲ.ሴ በ106 ኪሎ ፓስካል ግፊት ለ30 ደቂቃ መቀቀል ይኖርባቸዋል፡፡

እቃዎችን በአውቶክሌቭ ለመቀቀል በምንዘጋጅበት ጊዜ መደረግ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች

- እቃዎች ለመቀቀል ከመግባታቸው በፊት ታጥበው የፀዱና የደረቁ መሆን አለባቸው

❖ የመቀቀያ ደቂቃ የሚያዘው አውቶ ክሌቭ የሚፈለገውን ሙቀት (121ዲ.ሴ) እና ግፊት (106ኪ..ፓ/ ሲደርስ ነው

❖ ከፍተኛ ሙቀትን ሊቋቋሙ የማይችሉ እንደ ፕላስቲክነት ያላቸው እቃዎች ሙቀትን በሚቋቋሙ እቃዎች ውስጥ ገብተው መቀቀል አለባቸው

❖ እንፋሎት በደንብ እንዲያገኙ ክዳናቸው ተከፍቶ፣የሚችሉት ተፈታትተው መግባት አለባቸው

❖ ኢንፌክሽየስ እና አደገኛ ከሆኑ ነገሮች ጋር ንክኪ ያላቸው እቃዎች ለየብቻ መቀቀል ይኖርባቸዋል

❖ አውቶ ክሌቭ በትክክል መስራቱ በየጊዜው መረጋገጥ እና ጥገና የሚያስፈልገው ከሆነ ወዲያው መጠገን አለበት፡፡

### 3.4. የኃይማኖት ተቋማት የቆሻሻ አወጋገድ

የሐይማኖት ተቋማት በስፋት አማኞች የሚገኙበት ሥፍራ በመሆኑ  ትኩረት ተሰጥቶት መሰረታዊ የሆኑ ለንፅህና አጠባበቅ የሚያስፈልጉ እንደ ንፁህ ውኃ፣መፀዳጃ ቤት፣የእጅ መታጠቢያ፣የፍሳሽና ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ሊኖረው ይገባል፡፡

በመሆኑም የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ በራሷ የሚሟሉትን ማሟላት እና ከአቅሟ በላይ የሆኑትን ከሐይማኖት አባቶች፣ቀበሌው አስተዳደር፣ከህብረተሰቡ፣ከጤና ጣቢያውና ከሌሎች ድጋፍ ሊያደርጉ ከሚችሉ አካላት ጋር በመተባበር መሥራት ይጠበቅባታል፡፡

❖ የሐይማኖት ተቋማቱ ንፅህናው የተጠበቀ እና ሽታ እንዳይኖረው መከታተል

❖ የሚሰራ፣ንፅህናው የተጠበቀና ሁል ጊዜ ክፍት የሆነ መፀዳጃ ቤት መኖር አለበት

❖ የሚሰራ እና ንፅህናው የተጠበቀ የገላ መታጠብያ መኖር አለበት

❖ የሐይማኖት ተቋማቱ  የደረቅ እና ፈሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ጉድጓድ ሊኖረው ይገባል፡፡

❖ የቧንቧ ውኃ ከሌለ ከንፁህ ቦታ የተቀዳ እና በንፁህ እቃ የተቀመጠ ውኃ ሊኖር ይገባል፡፡

❖ የተጠበቀ የውሃ መገኛ ከሌለ የዝናብ ውሃን በንፁህ እቃ በማጠራቀም አክሞ መጠቀም ይገባል፡፡

# 4. የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራትና አተገባበር

### 4.1. ህብረተሰቡንና የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በመለየት ስለ ፓኬጁ ምንነትና አተገባበር ማስተዋወቅ እና ማነቃቃት

❖ ፓኬጁ የሚመለከታቸውንና ባለድርሻ አካላትን መለየት

❖ ውይይት በማድረግ መግባባት ላይ መድረስ

❖ የማህበረሰብ ንቅናቄ ማካሄድ

❖ የ1ለ5 እና የልማት ቡድን አመራሮች ውይይት ማካሄድ

## 4.2. ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር (ደረጃ ሶስት የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች፣ የልማት ቡድን መሪዎች ወዘተ) አስፈላጊ መረጃዎችን ማሰባሰብ

- ❖ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ማደራጀት
- ❖ በቀበሌው በሚገኙት ተቋማት በመዘዋወር የቅኝት ሥራ መሠራት
- ❖ በቅኝቱ መሠረት የተግባራት ቅደም ተከተል ማውጣት
- ❖ የተለዩትን ተግባራት ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ማጣጣም
- ❖ በተገኙት ግኝቶች መሰረት ማቀድ
- ❖ ከተቋማቱ ማህበረሰብ ጋር ውይይት ማካሄድና ቅድመ ዝግጅት ማድረግ
- ❖ ከውይይት በኋላ መረጃ መሰብሰብና ያለውን ወቅታዊ አድርጎ መጠቀም
- ❖ መረጃ ማሰባሰብ ፣ማጠናቀርና በሚከተለው መልክ መተንተን
    - ○ በቀበሌው የሚገኙ ተቋማት ብዛት
    - ○ የመፀዳጃ ቤት መኖሩን
    - ○ በትምህርት ቤት የመፀዳጃ ቤት መቀመጫ እና የተማሪ ጥምርታ
    - ○ በሁሉም ተቋማት የመፀዳጃ ቤቱ የንፅህና ሁኔታ
    - ○ በሁሉም ተቋማት መፀዳጃ ቤቱ በፆታ የተለየ መሆኑን
    - ○ በሁሉም ተቋማት የንፁህ ውሃ አቅርቦት መኖሩን
    - ○ በሁሉም ተቋማት የእጅ መታጠቢያ መኖሩን
    - ○ በሁሉም ተቋማት የደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ
    - ○ በትምህርት ቤት ሳኒተሽን/ዋሽ ክበባት መቋቋማቸውን

## 4.3. ውጤቱን ለሁሉም ተቋማት መግለጥና በጋራ የሥራ ዕቅድ ማውጣት

- ❖ ውጤቱን መግለጥና በውጤቱ ዙሪያ መወያየት
- ❖ መረጃውን መሠረት ያደረገና የተቋማቱን ማኅበረሰብ ያሳተፈ የሥራ ዕቅድ ማውጣት
- ❖ እንደ አስፈላጊነቱ የሳምንት፣ የወር፣ የሩብ ዓመት፣ የግማሽ ዓመትና የዓመት የሥራ ዕቅድ ማውጣት፣
- ❖ ዕቅዱ ሲታቀድ ሙያዊ ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ

## 4.4. ትምህርት ቤት ክበባት ማጠናከርና ከየተቋማቱ ለተውጣጡ ባለድርሻ አካላት ስልጠና መስጠት

- ❖ ለሥልጠናው የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችንና አጋዥ መሣሪያዎችን መለየትና ማዘጋጀት

- በመሥፈርቱ መሠረት ፈቃደኛ የሆኑ መምህራንና ተማሪዎችን መመልመል
- ከሰልጣኞች ጋር በሥልጠናው ዙሪያ ውይይት ማድረግ
- የሥልጠና ሥፍራና ጊዜ በጋራ መወሰን
- ሥልጠናውን ማካሄድ
- በየጤና ክበባትን ማጠናከር እና ማቋቋም
- ክበቡ ሊሰራበት የሚችላቸውን ዝርዝር ተግባራት ከተቋማቱ ማህበረሰብ ጋር ሆኖ ማዘጋጀት
- ለክበባት እንቅስቃሴ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ከድጋፍ ሰጭ አካላት ጋር በመሆን ማሟላት

## 4.5. ለፓኬጁ ሥራ ደጋፊ ሊሆኑ ከሚችሉ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ የጤና ልማት ሰራዊት፣ተቋማት፣ ማህበራዊ ተቋማት፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በቅንጅት መሥራት

- በቀበሌው የሚገኙትን አጋዦችን (ደጋፊዎችን) መለየት
- መስተዳድር - አስተዳደራዊ ድጋፍ እንዲሰጥ፣
- ትምህርት - ለመምህራንና ተማሪዎች ትምህርት በመስጠት የአካባቢውን ህብረተሰብ እንዲያስተምሩ፣ ለተማሪዎች የሚያስፈልጉ አገልግሎቶችን እንዲያሟሉ፣
- ወመህ - በትምህርት ቤቱ ውስጥ አገልግሎቶች እንዲሟሉ ድጋፍ በማድረግና በመከታተል
- መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች - መገልገያ ተቋማትና በማሟላት፣ በቴክኒክና በቁሳቁስ ወዘተ. በመደገፍ
- የ1ለ5 እና የልማት ቡድን መሪዎች -ለትምርት ቤት ማህበረሰብ ሙያዊ ድጋፍ እንዲያደረጉ መደገፍ
- የኃይማኖት ተቋማት- ለእምነቱ ተከታዮች እንዲያስተምሩና የሚያስፈልጉ አገልግሎቶችን እንዲያሟሉ
- ወፍጮ ቤቶች- ለደንበኞቻቸው የሚያስፈልጉ አገልግሎቶችን እንዲያሟሉ እና ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎችንና የጤና ጠንቆችን ለመቀነስ አስፈላጊ ርምጃዎችን እንዲወስዱ እንዲሁም ግለሰቦች ወፍጮ ቤት ለመትክል ሲያስቡ የጤና ባለሙያዋን እንዲያማክሩ
- ከላይ የተሰባሰበውን የመረጃ ውጤት መግለጥ፣ ውይይት ማካሄድና የጋራ ስምምነት ላይ መድረስ

## 4.6. ዕቅድ ማዘጋጀትና በትብብር መሥራት

- በአካባቢው በሚገኙ የጤና ተቋማት ውስጥ የሚሠሩ የጤና ባለሙያዎችን በማሳተፍ ሥራዎችን መሥራት
- እገዛ የሚያስፈልገውን ክፍተት መለየት

❖ የጤና ባለሙያዎችን ቴክኒካዊ እገዛ መጠየቅ

❖ በጋራ ተባብሮ መሥራት

## 4.7. የተቋማቱን ማህበረሰብ በመቀስቀስ፣በማስተማር፣ተሳትፎውን በማሳደግ ቀጣይ የጸባይ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ትምህርት ተግባራት በመለየት ማከናወንና ተከታታይነት ያለው ክትትልና ድጋፍ ማድረግ

❖ የጤና ትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት

❖ የትምህርት ርእሶች መለየት

❖ ትምህርቱ የሚሰጣቸውን ተቋማት መለየት

❖ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት/የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከላትን በመጠቀም

❖ ትምህርቱን መሥጠት፣ በተጨማሪም የት/ቤቶችን ሚኒ ሚድያ መጠቀም

## 4.8. ሠርቶ ማሳያ ዘዴ በመጠቀም ማህበረሰቡ በራሳቸው እንዲሠሩ ማስቻል

❖ በትምህርት ቤቶች ሰርቶ ማበልፀጊያ ማእከል በመጠቀም የሠርቶ ማሳያ እንዲሠሩ ማስቻል

❖ ፓኬጁን የተገበሩትን ተቋማት የተማሩትንና የተገበሩትን በማሳየት አጐራባች ተቋማት የራሳቸውን ሠርተው እንዲጠቀሙ ማድረግ

## 4.9. ምርጥ ተሞክሮ መለየት፣ መቀመርና ማስፋት

❖ በተቋማት ደረጃ

- ምርጥ ተሞክሮ ያላባቸውን አካባቢዎችንና ምርጥ ተሞክሮውን መለየት
- የተለዩትን ተሞክሮዎች መቀመር
- የተቀመሩትን ተሞክሮዎች የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ማስፋት

## 4.10. የማነቃቂያ ዘዴዎች በመጠቀም የማህበረሰቡን ባለቤትነት ማጠናከር

❖ በፖኬጁ ጥሩ ተሳትፎና እንቅስቃሴ ላደረጉ ተቋማት የማበረታቻ ስጦታዎች መስጠት

- የምስክር ወረቀት
- የመሥሪያ ቁሳቁስ - በአካባቢው በቀላሉ የሚገኝ
- በስብሰባ ላይ እንደ ምሳሌ መጥቀስ ወዘተ

## 4.11. አካባቢያዊና ሕጋዊ ደንቦችን መጠቀም

❖ የአካባቢያዊ ሕጐችን - ከመንግሥት ሕግና ደንቦች ጋር አጣጥሞ መሥራት፣

❖ ተቋማት በጋራ በሚወስነው መተዳደሪያ ደንብ እንዲያወጡ ማድረግ

❖ በመንግሥት የሚወጡ ህጐችን ተግባራዊ ማድረግ

### 4.12. የክትትልና የጉብኝት ሥራዎች ማካሄድ፣

❖ ፓኬጁ በአግባቡ መተግበሩን በሥፍራው በመገኘት ክትትል ማድረግና ሙያዊ ድጋፍ መሥጠት ይጠበቅባታል፡፡ይህም ማለት በተቋማት መፀዳጃ ቤት፣የእጅ መታጠቢያ፣ንፁህ ውሃ፣የእርጥብና ደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ፣በአግባቡ መያዛቸውንና መጠቀማቸውን እንዲሁም ማሻሻላቸውን መከታተል ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በወፍጮ ቤት ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎችንና የጤና ጠንቆችን ለመቀነስ  የሚያስችሉ ሥራዎች መሠራታቸውን መከታተል ያስፈልጋል፡፡

## 5. ከጤና ጣቢያ ጋር አብሮ መስራት

የጤና ጣቢያ ባለሞያዎች በተለይም የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ባለሙያ መረጃ አሰባሰብ፣ በቀበሌ ደረጃ ሊወጡ የሚገቡ ህጎችን በማርቀቅና ተሞክሮዎችን በመለየት በመቀመርና በማስፋት አብረው ያቅዳሉ ይሰራሉ፡፡ የልማት ቡድን አመራር ስልጠና ጊዜ ሙያዊ እገዛ ያደርጋሉ፡፡

## 6. የሚጠበቁ ውጤቶች

❖ በየተቋማቱ የሚገኙ ማህበረሰቦች ስለ ጤና ያላቸው ግንዛቤ ከፍ ይላል፡፡

❖ ንፁህና አደጋ የማያደርሱ ት/ቤቶች፣የሐይማኖት ተቋማት፣ወፍጮ ቤቶችና ጤና ኬላዎች ይኖራሉ

❖ በትምህርት ቤቶች፣በሐይማኖት ተቋማት፣ወፍጮ ቤቶች ለሴቶችና ለወንዶች የተለየ እና ንፅህናው የተጠበቀ መፀዳጃ ቤት ይኖራል፡

❖ ከመፀዳጃ ቤት መልስ እጅን የመታጠብ ልምድ በተማሪዎች፣በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብና በቤተሰቦቻቸው ይዳብራል፡፡

❖ በተማሪዎች፣የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብና በቤተሰቦቻቸው የንፁህ ውሃ አጠቃቀም ይዳብራል፡፡

❖ በትምህርት ቤትና በወፍጮ ቤት ውስጥ የሚከሰቱ ድንገተኛ አደጋዎች ለከፋ አደጋ ሳይደርሱ እርዳታ ያገኛሉ፣ወደ ጤና ተቋማትም ይላካሉ

❖ በት/ቤቶች ውስጥ የግል ንፅህና ይጠበቃል፣ተያያዥነት ያላቸው እንደ ትራኮማ፣የአንጀት ትላትል እና በሌሎች በሽታዎች የሚደርሰው ጉዳትና ስቃይ ይቀንሳል፣

❖ የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ይጨምራል

❖ በተቋማት ከዕቅድ ማውጣት እስከ ማስፈጸም ድረስ  የቅንጅታዊ አሰራር ባህል ይዳብራል

❖ በጤና ኬላ ጤናማ የህክምና ቆሻሻዎች አሰባሰብ፣አያያዝና አወጋገድ ስርአት ይፈጠራል/ የበሽታዎች መከላከል ሥርዓት ይጠናከራል፡፡

❖ የአካባቢ ብክለቶች ይቀንሳሉ

❖ ለፓኬጁ ትግበራ ድጋፍ የሚሰጡ ተጨማሪ የህብረተሰብ ክፍሎች ይፈጠራሉ፤

- ❖ የቅንጅታዊ አሠራር ባህል ይዳብራል
- ❖ ተቋማት ከተቋማት እውቀትና ልምድ በመቅሰም በራሳቸው አነሳሽነት የሚፈለግባቸውን ሥራ ያከናውናሉ፡፡
- ❖ ሞዴል ት/ቤቶች፣ጤና ኬላዎች እንዲሁም ተቋማት (ወፍጮ ቤት፣የሐይማኖት ተቋማት) ይፈጠራሉ፡፡

# 7. ክትትልና ግምገማ

## 7.1. ክትትል

ባለሙያዋ በክትትል ወቅት ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሁኔታዎች ትኩረት መስጠት ይገባታል፡:

- ❖ ት/ቤቶች፣የሐይማኖት ተቋማት እና ወፍጮ ቤቶች መፀዳጃ ቤት ሠርተው መጠቀማቸውን፣
- ❖ መፀዳጃ ቤቱ ንጹህ መሆኑን /የወለሉና ዙሪያው ዓይነ-ምድርና ሽንት አለመኖር/፣
- ❖ የመፀዳጃ ቤት መቀመጫ እና የተማሪ ጥምርታ መሟላቱን
- ❖ የመፀዳጃ ቤቱ የንፅህናው መጠበቁን
- ❖ መፀዳጃ ቤቱ በፆታ የተለየ መሆኑን
- ❖ የንፁህ ውሃ አቅርቦት መኖሩን
- ❖ የእጅ መታጠቢያ መኖሩን
- ❖ የወር አበባ ንፅህና አጠባበቅ በተመለከተ የተካሄዱ ዉይይቶች ብዛት
- ❖ የደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ ሁኔታ
- ❖ የጤና ክበባት መቋቋማቸውን እና እንቅስቃሴያቸውን
- ❖ ትምህርት ቤቶች፣ ወፍጮ ቤቶች እና የሐይማኖት ተቋማት በክትትል ወቅት በተሰጣቸው ትምህርትና ምክር መሰረት መሻሻላቸውን

## 7.2. ግምገማ

የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ በግምገማ ወቅት የምታተኩርባቸወ ነጥቦች:-

- ❖ የፕሮግራሙ አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎች፣
- ❖ ዓላማዎቹን ለማሳካት የተዘጋጁ ዝርዝር ዕቅዶች፣
- ❖ ዕቅዶቹን ለማስፈጸሚያ የዋሉ ግብዓቶች ማለትም
  - ○ የሰው ሀይል ብዛትና የሙያ ዓይነት
  - ○ የማቴሪያል /በአካባቢ የሚገኙ ቁሳቁሶችና ድጎማዎች

- የገንዘብ መጠን /ከህዝብ/ የተገኙትን በመለየት

- የግምገማ ማስፈጸሚያ ስልቶች
    - በመስክ በመዘዋወር ፣
    - ሪፖርቶችን በማሰባሰብና በመተንተን ፣
    - ተገልጋዮችን በማነጋገር፡፡
- የተከናወኑ ተግባራትን ለማወቅ የሚከተሉትን መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡
    - የሽፋን መለኪያዎች በመጠቀም/በፐርሰንት፣በቁጥር /በሬሺኦ/ ፣
    - የተገኙ ጠንካራ ጎኖች ፣ መልካም ተሞክሮዎች
    - የተገኙ ደካማ ጎኖች ፣
    - የተከናወኑ ተግባራት በህብረተሰቡ ጤና ላይ ያስከተለው ለውጥ ፣
    - ያጋጠሙ ችግሮች ፣
    - ችግሮቹን ለመፍታት የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

## 7.3. የፓኬጅ ጠቋሚዎች /indicators/

- መጸዳጃ ቤት ያላቸው ጤና ኬላዎች፣ት/ቤቶች፣የሐይማኖት ተቋማት እና ወፍጮ ቤቶች ብዛት
- መጸዳጃ ቤት ሠርተው የሚጠቀሙ ጤና ኬላዎች ፣ት/ቤቶች፣የሐይማኖት ተቋማት እና ወፍጮ ቤቶች ብዛት
- የተሻሻለ መጸዳጃ ቤት ያላቸው ጤና ኬላዎች፣ ት/ቤቶች፣የሐይማኖት ተቋማት እና ወፍጮ ቤቶች ብዛት
- የመፀዳጃ ቤት መቀመጫ እና የተማሪ ጥምርታ የተሟላላቸው ት/ቤቶች ብዛት
- መፀዳጃ ቤቱን በፆታ የለዩ ጤና ኬላዎች ፣ት/ቤቶች፣የሐይማኖት ተቋማት እና ወፍጮ ቤቶች ብዛት
- የንፁህ ውኃ አቅርቦት ያላቸው ጤና ኬላዎች፣ት/ቤቶች፣የሐይማኖት ተቋማት እና ወፍጮ ቤቶች ብዛት
- የእጅ መታጠቢያ ያላቸው ጤና ኬላዎች ፣ት/ቤቶች፣የሐይማኖት ተቋማት እና ወፍጮ ቤቶች ብዛት
- የደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ያላቸው ጤና ኬላዎች፣ ት/ቤቶች፣የሐይማኖት ተቋማት እና ወፍጮ ቤቶች ብዛት
- የጤና ክበባት የተቋቋመባቸው ት/ቤቶች ብዛት
- የእንግዴ ልጅ ማስወገጃና የቆሻሻ ማቃጠያ(Incinerator) ያላቸው ጤና ኬላዎች ብዛት

- ❖ ትምህርት ቤቶች፣ ወፍጮ ቤቶች እና የሐይማኖት ተቋማት በክትትል ወቅት በተሰጣቸው ትምህርትና ምክር መሰረት መሻሻላቸውን

<u>ማስታወሻ፡</u> **ይህን ክፍል በጤና መረጃ ሥርዓት ቅጽ ላይ (በዕቅድ፣ሪፖርት፣ክትትልና ግምገማ ማኑዋል ውስጥ) የተቀመጠውን ይጠቀሙ፡፡**